8ኛ ዓመት ቁጥር 4
8th Year No. 4

ባህር ዳር ጥር 25/1994 ዓ/ም
Bahir Dar February 2, 2003

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት

ዝክረ ህግ

ZIKRE HIG

Of the Council of the Amhara National Regional State in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Issued under the auspices of the Council of the Amhara National Regional State

✉ 1324
ያንዱ ዋጋ ብር 2.20
Unit price ---------

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 80/1995 ዓ/ም
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ገጠር መንገዶች ባለሥልጣንን እንደገና ማቋቋሚያ፣ ማደራጃና ሥልጣንና ተግባሩን መወሰኛ አዋጅ

Contents

Proclamation No. 80/2003
Re-establishment and Organization of the Amhara National Regional State Rural Roads Authority and Determination of its powers and Duties

አዋጅ ቁጥር 80/1995 ዓ.ም

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ገጠር መንገዶች ባለሥልጣንን እንደገና ለማቋቋም፣ ለማደራጀትና ሥልጣንና ተግባሩን ለመወሰን የወጣ አዋጅ

እስካሁን ድረስ ወንዙ የሚሠራበትን የክልሉን ገጠር መንገዶች ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 41/1991 ዓ.ም ተሻሽሎ ከወጣው የአማራ ብሔራዊ ክልል ሕገ መንግሥትና የብሔራዊ ክልላዊ መንግሥቱ አስፈፃሚ አካላት መልሶ ማደራጃና ሥልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 60/1994 ዓ.ም ድንጋጌዎች ጋር በተጣጣመ መንገድ በድጋሚ አሻሽሎ ማውጣት ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፤

የባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱን ውስጣዊ አደረጃጀትና የሥልጣን ድልድል ይበልጥ ግልጽና ለተጠያቂነትም ሆነ ለቀልጣፋ አሠራር በሚያመች አግባብ መደንገግ በማስፈለጉ፤

Proclamation No. 80/2003

A Proclamation to provide for the Re-establishment and Organization of the Amhara National Regional State Rural Roads Authority and the Determination of its powers and Duties

WHEREAS, it has become appropriate to re-amend the Regional Rural Roads Authority Establishment Proclamation No. 41/1999, which has to this day been in effect, in harmony with the Revised constitution of the Amhara National Region and the provisions of the Re-organization of the National Regional State Executive organs and determination of their powers and duties Proclamation No. 60/2001;

WHEREAS, it has become essential to proclaim the internal organization of the authority and the allocation of power inherent in it with full transparency, accountability and expeditious service delivery as a natural consequence thereof;

የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት በብሔራዊ ክልሉ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3/1/ ሥር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል::

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ " የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ገጠር መንገዶች ባለሥልጣን እንደገና ማቋቋሚያ፣ ማደራጃና ሥልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 80/1995 ዓ.ም " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ:-

1. "ገጠር መንገድ" ማለት የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን እንደገና በተቋቋመበት አዋጅ ቁጥር 80/1989 " አውራ ጎዳና " ብሎ ከሚሰይመውና በከተሞች አስተዳደር ከሚጠቃለለው መንገድ ውጪ ያለ ማናቸውም የገጠር መንገድ ነው::
2. " መንግሥት" ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ነው::
3. " ምክር ቤት" ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ነው::
4. " ቢሮ " ማለት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አስፈፃሚ አካላት ማደራጀና ሥልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 60/1994 መሠረት የተቋቋመው የገጠር ልማት ቢሮ ነው::
5. "የኮሚዩኒቲ መንገድ " ማለት ምክር ቤቱ በሚያወጣው ፖሊሲ መሠረት የአካባቢው ሕዝብ በገንዘብና በጉልበት ወይም በዕርዳታ የሚሠራውና የሚጠገነው መንገድ ነው::

NOW, THEREFORE, the Amhara National Regional Council, in accordance with the powers vested in it under Article 49 sub-article 3/1 of the National Regional Constitution, hereby proclaims as follows:

PART ONE

GENERAL

1. Short Title

This Proclamation may be cited as " The Re-establishment and organization of the Amhara National Regional State Rural Roads Authority and determination of its Powers and Duties Proclamation No. 80/2003."

2. Definitions

In this Proclamation, unless the context requires otherwise:

1. " Rural Road" means any Rural Roads out of 'High way' which is designated by Ethiopian Roads Authority Pursuant to the powers vested in it by its Re-establishment proclamation No. 80/1997 and do not be administed by cities.
2. " State" means the Amhara National Regional State.
3. " Council" means the Council of the Amhara National Regional Government
4. " Bureau" means Rural Development Bureau Established by the Organization of the Amhara National Regional State Executive organs and Determination of their Powers and Duties Proclamation No. 60/2001.
5. " Community Road" means a Road Constructed and maintained by the people of a certain environment with their own finance and labor or with assistance pursuant to a policy to be issued by the Council.

6. "ግንባታ" ማለት የመንገድ ኮንስትራክሽንና የማሻሻያ ሥራዎችን የሚያጠቃልል ተግባር ነው::

7. " የመንገድ ፈንድ " ማለት በፌዴራል መንግስት አዋጅ ቁጥር 66/1989 ዓ.ም የተቋቋመው ፈንድ ነው::

ክፍል ሁለት

ስለ ገጠር መንገዶች ባለሥልጣን እንደገና መቋቋም፣ ተጠሪነት፣ ዓላማ ፣ሥልጣን፣ አደረጃጀትና አመራር

3. መቋቋም

1. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የገጠር መንገዶች ባለሥልጣን /ከዚህ በኋላ " ባለሥልጣኑ " እየተባለ በዚህ አዋጅ የሚጠራ/ ራሱን የቻለና ሕጋዊ ሰውነት ያለው የክልሉ መንግሥት አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል::

2. የባለሥልጣኑ ተጠሪነት ለቢሮው ይሆናል::

4. ዋና መሥሪያ ቤት

የባለሥልጣኑ ዋና መሥሪያ ቤት በባህር ዳር ከተማ ሆኖ በክልሉ ውስጥ በተለያዩ ሥፍራዎች እንደ አስፈላጊነቱ ቅርንጫፍ፣ የተገናና ጊዜያዊ ፕሮጀክት ጽ/ቤቶች ይኖሩታል::

5. ዓላማዎች

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ዋና ዋና ዓላማዎች ይኖሩታል:-

1. ኢኮኖሚያዊ አዋጭነታቸውን ግምት ውስጥ በማስገባት በክልሉ ውስጥ የሚገኙ የገጠር መንገዶችን ግልግት፣ ማስተዳደርና የግንባታም ሆነ የጥገና ሥራዎች ወጥና ፍትሐዊ ሥርጭት ያላቸው መሆኑን ማረጋገጥ፤

2. የክልሉ ሕብረተሰብ በኮሚዩኒቲ መንገድ ግንባታና ጥገና ሥራዎች በቀጥታ የሚሣተፍበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር::

6. " Construction" means an activity encompassing construction and improvement of road.

7. " Road Fund" means the Fund established by the Federal Proclamation No.66/1997.

PART TWO

Re-establishment, Accountability, Objectives, Powers Organizational Structure and leadership of the Rural Road Authority

3. Establishment

1. The Rural Roads Authority of the Amhara National Regional state (hereinafter referred to as "authority") is hereby established as an autonomous Regional governmental institution under this proclamation.

2. The authority shall be accountable to the Bureau.

4. Head office

The Head office of the Authority shall be in Bahir Dar; Branch, Maintenance and Project offices however be established in other places as may be necessary.

5. Objectives

The authority shall have the following major objectives:

1. Taking into account the Economic feasibility, develope and administer rural roads in the region and to verify the consistency and fair distribution of the construction and maintenance of community roads;

2. Facilitate conducive atmosphere for the participation of the people in the construction and maintenance of community roads.

6. የባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባር

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

1. መንገዶችን የሚመለከቱ የፌዴራል መንግሥት ፖሊሲዎችና ሕጎችን በክልሉ ውስጥ ያስፈጽማል፣

2. የገጠርና የኮሚዩኒቲ መንገዶችን የሚመለከቱ ክልል አቀፍ ፖሊሲዎችን፣ ሕጎችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን ያመነጫል፣

3. የገጠር መንገዶች ፊዚቢሊቲ /አዋጭነት/ ጥናት ያካሂዳል፣ እንዲካሄዱ ያደርጋል፣

4. የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን የሚያወጣቸውን አገር አቀፍ የዲዛይን ደረጃዎች በመከተል ለክልሉ ገጠር መንገዶች የሚያስፈልጉትን ዲዛይኖች በብቁ አማካሪዎች አማካይነት ወይም በራሱ ያዘጋጃል፣

5. የገጠር መንገዶች ግንባታ በስራ ተቋራጮች እንዲካሄድ ያደርጋል፣ ሆኖም ይህ አማራጭ የማያዋጣ ሆኖ ሲያገኘው ወይም ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ግንባታውን ራሱ ያካሂዳል፣

6. የገጠር መንገዶችን በራሱ ኃይል ይጠግናል ወይም በሥራ ተቋራጮች ያስጠግናል፣

7. የግንባታና የአማካሪነት አገልግሎት ውሎችን ያዘጋጃል፣ እንዲዘጋጁ ያደርጋል ፣ይዋዋላል፣ ሥራዎች በውላቸው መሠረት የሚከናወኑ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ቁጥጥር ያደርጋል፣ በበላይነት ይመራል፣

8. የገጠር መንገዶች ዲዛይን፣ የኮንስትራክሽንና ቁጥጥር ሥራዎች ለሥራ ተቋራጮችና አማካሪዎች የሚሰጡበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ ሲሰጡም አፈጻጸማቸውን አግባብ ካለው አካል ጋር በመተባበር ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

9. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 8 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ:-

6. Powers and Duties of the Authority

The authority shall have the following powers and duties:

1. Cause the execution of policies and laws of the Federal state regarding roads in the Region;

2. Initiate Regional policies, laws, regulations and directives concerning rural and community roads;

3. Carry out and cause the carrying out of feasibility studies of rural Roads;

4. Prepare, using qualified consultants or by its own, designs for Rural Roads of the region in line with the standard design issued by Ethiopian Road Authority;

5. Construct rural roads through contractors, provided that it may undertake such works by its own force where contracting out of same is not feasible or pursuant to the directives of the Bureau issued thereof;

6. Maintain Rural Roads by its own force or through contractors;

7. Prepare, cause the preparation of and award construction and consultancy contracts; cause the supervision to ensure that works are executed as per terms of their respective contracts, and administer same;

8. Facilitate conditions for the rendering of the Design, construction and Inspections activities of Rural Roads to contracts and consultants; follow up and supervise implementation of same in collaboration with relevant body;

9. Without prejudice to the provisions of sub-article 8 of this Article:

ሀ. የገጠር መንገዶች ግንባታ ወይም ጥገና በራሱ ኃይል ወይም በጨረታ የሚከናወንበትን አማራጭ አያጠና ለቢሮው የውሣኔ ሃሳብ ያቀርባል፤

ለ. ለገጠር መንገዶች ግንባታ፣ ጥገና፣ ፊዚቢሊቲ ጥናት ዲዛይንና ግንባታ ቁጥጥር እንዳግባብነቱ የሚያስፈልጉ አማካሪ መሐንዲሶች የሚመረጡበትን ሁኔታ ይወስናል::

10. የኮሚዩኒቲ መንገዶችን በሚመለከት ሥራዎችን ያስተባብራል፣ ተፈላጊውን የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፤

11. የገጠርም ሆነ የኮሚዩኒቲ መንገዶች አስተማማኝ የመንገድ ጥገና እቅድ ተዘጋጅቶላቸው ወይም ብቁ የጥገና ኃይል ኖሯቸው እንዲሰሩ የሚያስችላቸውን መመሪያ በማዘጋጀት ለቢሮው ያቀርባል፣ ያስወስናል፣ የተወሰነውንም ያስፈፅማል፤

12. የገጠር መንገዶችን በሚመለከት የማቴሪያል ጥናት ያካሂዳል፣ እንዲካሄድ ያደርጋል፣ የተገኙ ጠቃሚ ውጤቶችንም በሥራ ላይ ያውላል፤

13. ለገጠር መንገዶች ልማትና ጥገና የሚያስፈልገውን የሰው ኃይል ያሰለጥናል፣ እንዲሰለጥን ያደርጋል፤

14. ከኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ጋር በመመካከር የክልሉን ገጠር መንገዶች በሚመለከት የትራፊክ መቆጣጠሪያ ምልክቶችን ወይም መሣሪያዎችን ዲዛይን ይሠራል፣ ባስፈላጊ የገጠር መንገዶችም ላይ ያኖራል፤

15. የሃገሪቱን የተሽከርካሪ ክብደትና መጠን ደንቦችና መመሪያዎች በገጠር መንገዶች ላይ ያስፈፅማል፤

A. Study and submit to the Bureau for approval, its recommendation concerning the alternatives of carrying out of the construction or maintenance of rural road with its own force, or through tender;

B. Decide the conditions of selecting consulting engineers, as the case may be, required for the construction, maintenance, feasibility study, design and supervision in respect of Rural Roads.

10. Coordinate and render technical services to the public with respect to community roads;

11. Prepare, submit and cause to be decided directives the Bureau by which both the rural and community road are to be carried out based on effective road maintenance plan or maintenance manpower; follow up its implementation up on approval;

12. Study or cause the study of materials concerning rural roads and apply thereof useful results;

13. Train or cause the training of man power necessary for development and maintenance of rural road;

14. Design, in consultation with the Ethiopian Roads Authority, traffic control posts and Devices relating to rural roads and place same on rural roads;

15. Enforce Vehicle weight and size regulations and directives of the country on Rural Roads;

ሀ. የገጠር መንገዶች ግንባታ ወይም ጥገና በራሱ ኃይል ወይም በጨረታ የሚከናወንበትን አማራጭ አያጠና ለቢሮው የውሣኔ ሃሳብ ያቀርባል፤

ለ. ለገጠር መንገዶች ግንባታ፣ ጥገና፣ ፊዚቢሊቲ ጥናት ዲዛይንና ግንባታ ቁጥጥር እንዳግባብነቱ የሚያስፈልጉ አማካሪ መሐንዲሶች የሚመረጡበትን ሁኔታ ይወስናል::

10. የኮሚዩኒቲ መንገዶችን በሚመለከት ሥራዎችን ያስተባብራል፣ ተፈላጊውን የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፤

11. የገጠርም ሆነ የኮሚዩኒቲ መንገዶች አስተማማኝ የመንገድ ጥገና እቅድ ተዘጋጅቶላቸው ወይም ብቁ የጥገና ኃይል ኖሯቸው እንዲሰሩ የሚያስችላቸውን መመሪያ በማዘጋጀት ለቢሮው ያቀርባል፣ ያስወስናል፣ የተወሰነውንም ያስፈፅማል፤

12. የገጠር መንገዶችን በሚመለከት የማቴሪያል ጥናት ያካሂዳል፣ እንዲካሄድ ያደርጋል፣ የተገኙ ጠቃሚ ውጤቶችንም በሥራ ላይ ያውላል፤

13. ለገጠር መንገዶች ልማትና ጥገና የሚያስፈልገውን የሰው ኃይል ያሰለጥናል፣ እንዲሰለጥን ያደርጋል፤

14. ከኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ጋር በመመካከር የክልሉን ገጠር መንገዶች በሚመለከት የትራፊክ መቆጣጠሪያ ምልክቶችን ወይም መሣሪያዎችን ዲዛይን ይሠራል፣ ባስፈላጊ የገጠር መንገዶችም ላይ ያኖራል፤

15. የሃገሪቱን የተሽከርካሪ ክብደትና መጠን ደንቦችና መመሪያዎች በገጠር መንገዶች ላይ ያስፈፅማል፤

A. Study and submit to the Bureau for approval, its recommendation concerning the alternatives of carrying out of the construction or maintenance of rural road with its own force, or through tender;

B. Decide the conditions of selecting consulting engineers, as the case may be, required for the construction, maintenance, feasibility study, design and supervision in respect of Rural Roads.

10. Coordinate and render technical services to the public with respect to community roads;

11. Prepare, submit and cause to be decided directives the Bureau by which both the rural and community road are to be carried out based on effective road maintenance plan or maintenance manpower; follow up its implementation up on approval;

12. Study or cause the study of materials concerning rural roads and apply thereof useful results;

13. Train or cause the training of man power necessary for development and maintenance of rural road;

14. Design, in consultation with the Ethiopian Roads Authority, traffic control posts and Devices relating to rural roads and place same on rural roads;

15. Enforce Vehicle weight and size regulations and directives of the country on Rural Roads;

16. የገጠር መንገዶችን ከጉዳትና አግባብ ካልሆነ አጠቃቀም ይጠብቃል፣ በገጠር መንገዶች የሚከሰቱ እንቅፋቶችን ያስወግዳል፣ እንዲወገዱ ያደርጋል፤

17. በገጠር መንገዶች ግራና ቀኝ እንዲሁም በአካባቢው ለሥራው የሚያስፈልገውን የመሬት መጠንና ሌሎች ሰዎች በዚሁ መሬት የሚጠቀሙበትን ሁኔታ ሥልጣን ላለው የመንግሥት አካል በማቅረብ ያስወስናል፤

18. ለገጠር መንገዶች ግንባታና ጥገና እንዲሁም ለመኖሪያ፣ ለመሣሪያ ማሣረፊያና ለሌሎች አገልግሎቶች የሚያስፈልገውን መሬትና ድንጋይ ነክ ሀብቶች በነፃ ይጠቀማል፤ ለመንገድ ግንባታና ለሌሎች አገልግሎቶች በሚጠቀምበት መሬት ላይ ለሚገኙ ንብረቶች በሕግ መሠረት ካሣ ይከፍላል፤

19. ማንኛውም ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው ድርጅት ለልዩ ወይም ለጋራ ዓላማና አገልግሎት የሚሠራውን፣ የሚጠግነውንና የሚያስተዳድረውን መንገድ ደረጃውን ጠብቆ ሲያገኘው ይረከባል፣ ይመዘግባል፤

20. በዚህ አዋጅ መሠረት ሥልጣንና ተግባሩን በሥራ ላይ በሚያውልበት ጊዜ የተፈጥሮና ማህበራዊ አካባቢ ደህንነት እንዲጠበቅ የሚያስፈልጉትን ጥንቃቄዎች ያደርጋል፤

21. የሥራ እንቅስቃሴውን በሚመለከት በየወቅቱ ለቢሮው ሪፖርት ያቀርባል፤

22. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፤

23. ከዚህ አዋጅና ከሌሎች ሕጎች ጋር የማይቃረኑ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል።

16. Protect rural Roads from damage and abuse, remove and cause the removal of obstructions from Rural roads;

17. Submit to the authorized body for approval the extent of land required for its activities in the adjacency as well as surrounding of Rural Roads and the conditions of use of such land by others;

18. Use, free of charge, land and such other resources and quarry substances required for the purpose of construction and maintenance of rural Road and camp, storage of equipment and other required services; provided, however, it shall pay compensation in accordance with law for any property found on the land;

19. Posses and Register, when it finds up to the standard, the road constructed, maintained and administered by any physical or juridical organization for special or common objective and service;

20. Take necessary means so that natural and social environmental protections are to be protected when it implements its powers and duties vested in it under this Proclamation;

21. Submit a report, in due time, to the Bureau concerning its work activities;

22. Own property, enter into contract, sue and be sued in its own name;

23. Perform other duties which are not inconsistent with the provisions of this proclamation and other laws.

7. ድርጅታዊ አቋም

ባለሥልጣኑ አላማውን ከግብ ለማድረስ የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል፦

1. በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር የሚሾሙ አንድ ዋና ሥራ አስኪያጅና ምክትል ሥራ አስኪያጅ፣

2. ለሥራው የሚያስፈልጉ የበታች የሥራ ኃላፊዎችና ሌሎች ሠራተኞች።

7. Organizational structure

The Authority, to achieve its objectives, shall have:

1. A General manager and Deputy manager to be appointed by the Head of the Regional Government;

2. Necessary lower officials and staffs.

8. ስለ ባለሥልጣኑ አመራር

1. ባለሥልጣኑ በአንድ ዋና ሥራ አስኪያጅ ይመራል፣ ይተዳደራል፤
2. የዋና ሥራ አስኪያጁ ተጠሪነት ለቢሮውና ለርዕሰ መስተዳድሩ ይሆናል።

9. የዋናው ሥራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባር

የባለሥልጣኑ ዋና ሥራ አስኪያጅ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 ሥር የተጠቀሱትን የባለሥልጣኑን ሥራዎች በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፤
2. በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 42/1985 ዓ.ም /እንደተሻሻለ/ መሠረት የባለሥልጣኑን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፤
3. ቢሮው በሚያወጣው አስተዳደራዊ መመሪያ መሠረት የባለሥልጣኑን የሥራ መሪዎች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፤
4. ባለሥልጣኑ ለሥራው አፈፃፀም የሚመራባቸውን ልዩ ልዩ መመሪያዎች ያዘጋጃል፣ ሲፀድቁም ሥራ ላይ ያውላል፤
5. የባለሥልጣኑን የአጭር፣ የመካከለኛና የረዥም ጊዜ እቅዶችና የሥራ ፕሮግራሞች እንዲሁም የማስፈፀሚያ በጀታቸውን ረቂቅ ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤
6. አስቀድመው በፀደቁ የባለሥልጣኑ ፕሮግራሞችና በጀት መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤
7. የቢሮውንና የምክር ቤቱን ውሣኔዎች ይፈፅማል፣ ያስፈፅማል፤
8. የባለሥልጣኑን የሥራ አፈፃፀም፣ የሂሣብ መግለጫዎችና የአዲት ሪፖርቶች በወቅቱ ለቢሮው ያቀርባል፤
9. ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ባለሥልጣኑን ይወክላል።

8. Leadership of the Authority

1. The Authority shall be led and administered by the General manager;
2. The General manager shall be accountable to the Bureau and the Head of the Regional Government.

9. Powers and Duties of the General Manager

The General manager shall have the following powers and Duties:

1. Direct and coordinate the activities of the Authority stated under Article 6 of this proclamation;
2. Employ, administer and dismiss its employees in accordance with the labour proclamation No.42/1993 (as amended);
3. Employ, administer and dismiss officials of the authority pursuant to the Administrative directives issued by the Bureau;
4. Prepare directives, by which the Authority is guided and implement same upon approval;
5. Prepare the short, medium and long term plan, work programs and budget of the Authority; implement same upon approval;
6. Effect expenditure, in accordance with the approved budget and plan of action of the authority;
7. Execute and cause the execution of the decision of the Bureau and the council;
8. Prepare and submit to the Bureau activity performances, financial explanations and audit reports of the authority;
9. Represent the authority in its dealings with other third parties.

10. የምክትል ሥራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባር

የባለሥልጣኑ ምክትል ሥራ አስኪያጅ ተጠሪነቱ ለዋናው ሥራ አስኪያጅ ሆኖ:-

1. በዋናው ሥራ አስኪያጅ ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፤
2. ዋናው ሥራ አስኪያጅ በማይኖርበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜና ሁኔታ አርሱን ተክቶ ይሠራል::

ክፍል ሶስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

11. የገቢ ምንጭ

የባለሥልጣኑ ገቢ ከሚከተሉት ምንጮች የሚገኝ ይሆናል፤

1. የክልሉ መንግሥት የሚመድበው በጀት፣
2. የመንገድ ፈንድ፣ እና
3. ሌሎች ምንጮች::

12. የሂሣብ መዛግብትና አዲት

1. ባለሥልጣኑ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል፤
2. የባለሥልጣኑ የሂሣብና ገንዘብ ነክ ሠነዶች በክልሉ ዋና አዲተር ወይም አርሱ በሚሰይመው ሌላ አዲተር በየጊዜው ይመረመራሉ::

13. የቴክኒክ ምርመራ

ባለሥልጣኑ በአያንዳንዱ የግንባታና የጥገና ሥራዎች ላይ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ የቴክኒክ ምርመራ ያከናውናል::

14. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

ቢሮው ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉትን ልዩ ልዩ መመሪያዎች ሊያወጣና በሥራ ላይ ሊያውል ይችላል::

10. Powers and Duties of the Deputy Manager

The Deputy manager, with his accountability being to the General Manager, shall:

1. Undertake such duties as may specifically be rendered to him by the General Manager;
2. Perform, in the capacity of the General manager, in case of absence or inability of the latter to discharge his duties.

PART THREE

Miscellaneous Provisions

11. Source of Finance

The Authority shall be financed from the following sources:

1. Budget allocated by the Regional Government;
2. Allocations from the Road fund, and
3. Other sources.

12. Books of Accounts and Auditing

1. The Authority shall keep complete and accurate books of accounts.
2. The Accounts and financial documents of the authority shall be audited, on due time, by the Auditor General of the Region or by auditors designated by him.

13. Technical Examination

The authority shall undertake technical examination on each construction and maintenance works at least once in a year.

14. Powers to Issue Directives

The Bureau may issue directives necessary for the implementation of this proclamation.

15. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት በባለሥልጣኑ የሥራ አመራር ቦርድ የፀደቁና ባለሥልጣኑ የሚሠራባቸው የሰው ኃይል አስተዳደር፣ የፋይናንስ፣የግዥና ሌሎች መመሪያዎች በቢሮው እየተመረመሩ በአዲስ አስኪተኩ ወይም አስኪሻሻሉ ድረስ ከዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ጋር አለመቃረናቸው እየታየ ተፈፃሚነታቸው ይቀጥላል::

16. የተሻሩና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች

1. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ገጠር መንገዶች ባለሥልጣን እንደገና የተቋቋመበት አዋጅ ቁጥር 41/1991 ዓ.ም ተሽሮ በዚህ አዋጅ ተተክቷል፣

2. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ አዋጅ ውስጥ በተሸፈኑት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም::

17. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከጥር 25 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል::

ባህር ዳር
ጥር 25 ቀን 1995 ዓ.ም

ዮሴፍ ረታ
የአማራ ብሔራዊ ክልል
ፕሬዚዳንት

15. Transitory Provision

Human resource administration, finance, Purchasing and other directives approved by the board of the authority, before the coming in to force of this proclamation, shall continue to be applied so long as they do not contravene the Provisions of this Proclamation.

16. Replaced and Inapplicable Laws

1. A Proclamation (No. 41/1999) to provide for the Re-establishment of Rural Roads Authority of the Amhara National Regional State is hereafter repealed and be replaced by this Proclamation.

2. Any Law, Regulation, Directive, or Practices inconsistent with this Proclamation shall not be applicable on matters provided in this Proclamation.

17. Effective Date

This Proclamation shall come into force as of Feb.2,2003.

Done at Bahir Dar,
This 2nd day of February 2003.

Yosef Retta
President of the Amhara National
Regional State